ቁጥር/Ref.No. ሲሰ ክ30/ጠ13/1882/14

በዝርዝሩ ለተመለከቱት የመንግሥት ተቋማት በሙሉ
ባሉበት

ቀን/ Date 15 ሐምሌ 2014

ጉዳዩ፡- <u>የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ መመሪያን ይመለከታል፡፡</u>

የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ስለክፍያው መጠን እና የማካካሻ እረፍት ስለሚሠጥበት ሁኔታ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 35 መሠረት መመሪያ እንደሚወጣ መደንገጉ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በአዋጁ አንቀጽ 97 ንኡስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተዘጋጀውን የአፈፃፀም መመሪያ ከዚህ መሸኛ ጋር አያይዘን መላካችንን እየገለጽን፣ መመሪያው ከነሐሴ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እናሳውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>
- ለክቡር ኮሚሽነር
- ለክብርት ም/ኮሚሽነር
- ለክቡር ም/ኮሚሽነር
- ለክቡር ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለአደረጃጀት የሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት
- <u>ሲ.ሰ.ኮሚሽን</u>

ስልክ/Tel: +251 115 54 96 66/67
ፋክስ/Fax: +251 115549707
Email: contactus@ecsc.gov.et
Website:- www.ecsc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

| ተ.ቁ | መስሪያ ቤት ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 1 | **ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት** | አዲስ አበባ |
| 2 | ኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 3 | ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 4 | ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 5 | ኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም | አዲስ አበባ |
| 6 | ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 7 | ፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት | አዲስ አበባ |
| 8 | **ፌደሬሽን ምክር ቤት** | አዲስ አበባ |
| 9 | ሕገመንግሥት አጣሪ ጉባዔ ጽ/ቤት | አዲስ አበባ |
| 10 | ህገ መንግስትና ፌዴራሊዝም አስተዳደር ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 11 | **ፕሬዘዳንት ጽሕፈት ቤት** | አዲስ አበባ |
| 12 | **ጠቅላይ ሚኒስትር ፅህፈት ቤት፣** | አዲስ አበባ |
| 13 | ኢትዮጵያ ንሽስትመንት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 14 | ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 15 | ኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ተጠሪነት | አዲስ አበባ |
| 16 | አፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 17 | ቤተ-መንግሥት አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 18 | ኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 19 | ኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 20 | ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 21 | ፋይናንስ ደህንነት መረጃ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 22 | አርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 23 | አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 24 | ሪፐብሊኩ ጥበቃ ኃይል | አዲስ አበባ |
| 25 | ፌዴራል ሥነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 26 | መንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 27 | ግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 28 | መንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 29 | ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 30 | **ሰላም ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 31 | **መከላከያ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 32 | **ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 33 | ውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 34 | ኢትዮጵያ ዳያስፓራ ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 35 | **ገንዘብ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 36 | ኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ | አዲስ አበባ |
| 37 | መንግስት ግዢ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 38 | መንግሥት ግዢና ንብረት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 39 | መንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ | አዲስ አበባ |
| 40 | **ፍትህ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 41 | ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 42 | ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 43 | ፌደራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |

| ተ.ቁ | መስሪያ ቤት ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 44 | ሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 45 | ፌደራል ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ | አዲስ አበባ |
| 46 | ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 47 | ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 48 | ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 49 | ጠቅላይ ሸሪያ ፍርድ ቤት | አዲስ አበባ |
| 50 | ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ | አዲስ አበባ |
| 51 | ዕርቀ ሰላም ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 52 | አስተዳር ጉዳዮች፣ ወሰንና ማንነት ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 53 | **ግብርና ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 54 | ኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 55 | ኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | አዲስ አበባ |
| 56 | ኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 57 | ኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 58 | ኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 59 | እንስሳት ጤና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 60 | እንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 61 | ኢትዮጵያ ደን ልማት | አዲስ አበባ |
| 62 | ኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 63 | **ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 64 | አምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 65 | ኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት | አዲስ አበባ |
| 66 | **ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 67 | ኢትዮጵያ ደረጃዎች ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 68 | ኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 69 | ኢትዮጵያ አክሬዲቴሽን አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 70 | ነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 71 | ኢትዮጵያ ተስማሚነት ምዘና ድርጅት | አዲስ አበባ |
| 72 | **ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 73 | ኢመርጂንግ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 74 | ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 75 | ስፔስ ቴክኖሎጂና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 76 | ኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 77 | **ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 78 | ኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 79 | ኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 80 | መድን ፈንድ አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 81 | ፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፓርት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 82 | **ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 83 | ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲቲዩት | አዲስ አበባ |
| 84 | ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 85 | ኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 86 | **ውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |

| ተ.ቁ | መስሪያ ቤት ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 87 | ኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 88 | ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 89 | ታላቁ ሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት | አዲስ አበባ |
| 90 | **መስኖና ቆላማ አካባቢ ልማት ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 91 | **ማዕድን ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 92 | ኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 93 | ማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 94 | **ጤና ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 95 | ቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 96 | ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታልና ሚሊኒም ሜዲካል ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 97 | አማኑኤል አዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 98 | ገፈርሳ አእምሮ ህሙማን ማገገሚያ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 99 | መላ አፍሪካ ስጋ ደዌ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 100 | ኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 101 | ኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 102 | ኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ድርጅት | አዲስ አበባ |
| 103 | ኢትዮጵያ ጤና መድን አስተዳደር | አዲስ አበባ |
| 104 | ኢትዮጵያ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 105 | አርማወር ሐንሰን ምርምር ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 106 | ኤካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 107 | ኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 108 | አቤት ሆስፒታል | አዲስ አበባ |
| 109 | **ቱሪዝም ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 110 | ኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 111 | ኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 112 | **ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 113 | ስፖርት አካዳሚ | አዲስ አበባ |
| 114 | ጥሩነሽ ዲባባ አትሌቲክስ ማሰልጠና ማዕከል | አዲስ አበባ |
| 115 | ኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 116 | ኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻህፍት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 117 | ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር | አዲስ አበባ |
| 118 | **ገቢዎች ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 119 | ኢትዮጵያ ጉሙሩክ ባለሥልጣን | አዲስ አበባ |
| 120 | **ፕላንና ልማት ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 121 | ኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 122 | ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 123 | አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን | አዲስ አበባ |
| 124 | **ሴቶች ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 125 | **ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር** | አዲስ አበባ |
| 126 | ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 127 | አጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 128 | አላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 129 | አርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አዲስ አበባ |

| ተ.ቁ | መስሪያ ቤት ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 130 | ገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 131 | ሚዛን ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ | አዲስ አበባ |
| 132 | ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት | አዲስ አበባ |
| 133 | ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 134 | ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 135 | ስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 136 | ትምህርት ሚኒስቴር | አዲስ አበባ |
| 137 | አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 138 | አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | አዳማ |
| 139 | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ | አዲስ አበባ |
| 140 | ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ | ሀሮማያ |
| 141 | ጅማ ዩኒቨርሲቲ | ጅማ |
| 142 | አምቦ ዩኒቨርሲቲ | አምቦ |
| 143 | ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ | ሃዋሳ |
| 144 | መቐሌ ዩኒቨርሲቲ | መቐሌ |
| 145 | ዲላ ዩኒቨርሲቲ | ዲላ |
| 146 | ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ | ባህር ዳር |
| 147 | አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ | አርባ ምንጭ |
| 148 | ጎንደር ዩኒቨርሲቲ | ጎንደር |
| 149 | ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ | ሶዶ |
| 150 | መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ | ሮቤ |
| 151 | ወለጋ ዩኒቨርሲቲ | ነቀምቴ |
| 152 | ጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ | ጅግጅጋ |
| 153 | ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ | ድሬዳዋ |
| 154 | ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ | ደብረብርሃን |
| 155 | ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ | ወልዲያ |
| 156 | አዲግራት ዩኒቨርሲቲ | አዲግራት |
| 157 | ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ | ደብረ ታቦር |
| 158 | አሶሳ ዩኒቨርሲቲ | አሶሳ |
| 159 | ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርሲቲ | ሚዛን |
| 160 | ወሎ ዩኒቨርሲቲ | ደሴ |
| 161 | አክሱም ዩኒቨርስቲ | አክሱም |
| 162 | ሰመራ ዩኒቨርስቲ | ሰመራ |
| 163 | ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ | ደብረማርቆስ |
| 164 | ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ | ሆሳዕና |
| 165 | ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ | ወልቂጤ |
| 166 | ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ | ቡሌ ሆራ |
| 167 | መቱ ዩኒቨርሲቲ | መቱ |
| 168 | ጋምቤላ ዩኒቨርስቲ | ጋምቤላ |
| 169 | አርሲ ዩኒቨርስቲ | አሰላ |
| 170 | አዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ | ጭሮ |
| 171 | መቅደላ አምባ ዩንቨርስቲ | መቅደላ |
| 172 | ሰላሌ ዩኒቨርስቲ | ፍቼ |

| ተ.ቁ | መስሪያ ቤት ስም | አድራሻ |
|---|---|---|
| 173 | ደንቢዶሎ ዩኒቨርስቲ | ደንቢዶሎ |
| 174 | እንጅባራ ዩኒቨርስቲ | እንጅባራ |
| 175 | ደባርቅ ዩኒቨርስቲ | ደባርቅ |
| 176 | ራያ ዩኒቨርስቲ | ራያ |
| 177 | ወራቤ ዩኒቨርስቲ | ወራቤ |
| 178 | ቀብሪደሀር ዩኒቨርስቲ | ቦንጋ |
| 179 | ቦንጋ ዩኒቨርስቲ | ቀብሪደሃር |
| 180 | ጂንካ ዩኒቨርስቲ | ጂንካ |
| 181 | ቦረና ዩኒቨርስቲ | ያቤሎ |
| 182 | ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 183 | ኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርስቲ | አዲስ አበባ |
| 184 | ትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት | አዲስ አበባ |
| 185 | ትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን | አዲስ አበባ |

# የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀድበት፣ የክፍያው መጠን እና ማካካሻ እረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ መመሪያ ቁጥር 921/2014

ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ሐምሌ 2014 ዓ/ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 35 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀዱባቸው ሁኔታዎች፣ ስለክፍያው መጠን እና የማካካሻ እረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይህን የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል 1

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀዱባቸው ሁኔታዎች፣ ስለክፍያው መጠን እና የማካካሻ እረፍት ስለሚሰጥበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ ቁጥር 921/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

**የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-**

1/ **"አዋጅ"** ማለት የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ሲሆን በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2/ **"ደንብ"** ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 502/2014 ነው፡፡

3/ **"ኮሚሽን"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአስፈፃሚ አካላትን ተግባርና ሃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 42 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የተቋቋመ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡

4/ **"የበላይ ኃላፊ"** ማለት የመንግስት መ/ቤትን በበላይነት የሚመራ ኃላፊ ነው፡፡

ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

5/ **"የመንግሥት ሠራተኛ"** ማለት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው እና በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባህርይ በሌለው ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት/ኮንትራት/ ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው፡፡

6/ **"መደበኛ የስራ ጊዜ"** ማለት በቀን 8 ሰዓት እና በሣምንት 39 የሥራ ሰዓት ማለት ነው፡፡

7/ **"የትርፍ ሰዓት ሥራ"** ማለት በመንግሥት መ/ቤት ከመደበኛው የሥራ ሰዓት ውጭ የሚሠራ ሥራ ነው፡፡

8/ **"የትርፍ ሰዓት ሥራ የክፍያ ሂሣብ ስሌት"** ማለት ሠራተኛው በመደበኛው የሥራ ሰዓት ከተተመነው የሚታሰብ ስሌት ነው፡፡

9/ **"የትርፍ ሰዓት ክፍያ"** ማለት መንግሥት በሕግ ካወጣው መደበኛ የሥራ ሰዓት በላይ ለተከናወነ ሥራ በሰዓት ታስቦ ለሠራተኛው የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡

10/**"መደበኛ የሥራ ሰዓት"** ማለት የመንግሥት ሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት እንደሥራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሳምንት 39 የሥራ ሰዓት ነው፡፡

11/**"የማካካሻ ዕረፍት"** ማለት የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሠራ የመንግሥት ሠራተኛ የሚሰጥ ዕረፍት ነው፡፡

12/ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## 3. የመመሪያው ዓላማ

በሥራ ባህርያቸው ምክንያት ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ ባስገዳጅ ምክንያት በመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚሠሩ ሥራዎችን በጊዜውና በተቀላጠፈ ሁኔታ በማሠራት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲወጡ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና በመንግስት በጀት በሚተዳደሩ መንግስት መ/ቤቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

# ክፍል 2

## የመንግሥት መሥሪያ ቤት የትርፍ ሰዓት ሥራ አፈቃቀድና የሚጠበቁ ኃላፊነቶች

5. የትርፍ ሰዓት ሥራ ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች፡-

1/ የማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሥራ የሥራው ባህርይ ካላስገደደ በስተቀር ዝርዝር ዕቅድ ወጥቶለት በዕቅዱ መሠረት በመደበኛ የሥራ ሰዓት ተከናውኖ መጠናቀቅ አለበት፡፡

2/ በማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የትርፍ ሰዓት ሥራ ተግባራዊ የሚሆነው በመንግስት መ/ቤት የበላይ ኃላፊ አስቀድሞ ከተፈቀደ ብቻ ነው፡፡

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት፡-

ሀ. በድንገት የተከሰተን ልዩ ሁኔታ ለመቋቋም ወይም ሊደርስ የሚችል ጥፋትን ለመከላከል የሚያስገድድ ሁኔታ ሲፈጠር፣

ለ. የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአቅሙ በላይ የሆነ ልዩ ሁኔታ ገጥሞት ሠራተኛውን ለማሰራት ሲፈልግ፣

ሐ. ከጊዜ ገደብ ጋር በተያያዘ በመደበኛ የሥራ ጊዜ ሊጠናቀቅ የማይችል አስቸኳይ ሥራ ሲያጋጥም፣

መ. የሥራ ብዛትና የሰው ኃይል ባለመመጣጠናቸው የተነሳ በጊዜ ተገድቦ መጠናቀቅ ያለበትን ሥራ ለማጠናቀቅ፣

ሰ. በመሥሪያ ቤቱ ልዩ የሥራ ባህርይ ምክንያት የሚፈጠሩ አስገዳጅ ሥራዎችን ለማከናወን፣

ረ. ሊቋረጥ በማይችል ተከታታይ ሥራ ላይ ከሥራ የቀሩ ሠራተኞችን ለመተካት፣ የላባራቶሪ፣ የማስኮብኘት ሥራ፣ የጉምሩክ እና ተመሳሳይ ሥራዎችን ለማከናወን፣

የትርፍ ሰዓት ሥራ ማሠራት ይቻላል፡፡

ሙኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

## 6. እንደትርፍ ሰዓት ሥራ የማይቆጠሩ ሥራዎች፡-

1/ የመስክ ሥራ በቀን የውሎ አበል ስለሚሸፈን፣ በመስክ ሥራ ምክንያት በመደበኛ ሥራ ላይ፣ ጉዞም ሆነ በመስክ ቆይታ የባከነ ሰአት ለማካካስ እና የሚያጋጥም ትርፍ ሥራን ማከናወን፣

2/ ማንኛውም የምርምር ስራ በባህርይው በማንኛውም ቀንና ሰዓት የሚሠራ ተግባር በመሆኑ፣

3/ በተረኛነት የአበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የሚስተናገድ የጤና ባለሙያዎች የሥራ ክንውን፣

4/ ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጭ የሚሰጥ ሥልጠና፣

5/ አግባብ ባለው የበላይ ኃላፊ ሳይፈቀድ ከመደበኛው የሥራ ሰዓት ውጭ የተከናወነ ስራ፣

6/ ሹፌሮች በማንኛውም ጊዜ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣ በየወሩ ከመደበኛ ደመወዝ ጋር በቁርጥ አበል የሚሰጣቸው ክፍያ የትርፍ ሰዓት ማካካሻ ታሳቢ ታደርጎ ስለሆነ ተጨማሪ የትርፍ ሠዓት ሥራ ክፍያ አይከፈልም፣

7/ በሥራ ባህርያቸው ምክንያት በሌሊት፣ በሳምንት የእረፍት ቀናት ወይም በበዓላት ቀን በመደበኛ የሽፍት ፕሮግራም የተከናወኑ ሥራዎች ናቸው፡፡

## 7. የትርፍ ሰዓት ጥያቄ አቀራረብ፡-

1/ ማንኛውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች አንዱ ተፈጥሮ በሥሩ ያሉ ሠራተኞች የትርፍ ሰዓት ሥራ መሥራት እንዳለባቸው ሲገነዘብ፣ ጥያቄውን ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ በጽሁፍ ያቀርባል፡፡

2/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲፈቀድ ጥያቄ ሲቀርብ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሊታዩ ይገባል፡-

ሀ. ሥራው በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሊሠራ ያልቻለበት ምክንያት፣

ለ. በትርፍ ሰዓት እንዲሠሩ የሚፈለጉ ሠራተኞች ብዛትና የስም ዝርዝር፣

ሐ. ሠራተኞቹ የተመደቡባቸው የሥራ መደቦች መጠሪያና ደረጃዎች፣

መ. የሠራተኞች የወር ደመወዝ፣

ሰ. የትርፍ ሰዓት ሥራ የሚጀምርበትና የሚያልቅበት ጊዜ እንዲሁም ሥራው ከሰባት የሥራ ቀናት በላይ የሚወስድና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚጠናቀቅ ከሆነ የሥራ ክንውኑን ሂደት የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ፣

ተብራርቶ መገለጽ አለበት፡፡

8. **የማንኛውም መንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊነት፡-**

1/ የትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲሠራ ሲፈቅድ፣ ሥራው በአነስተኛ የሰው ኃይልና ወጭ የሚከናወንበትን ስልት ይቀይሳል፡፡

2/ በትርፍ ሰዓት እንዲከናወን የተፈቀደው ሥራ ውጤትና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት መጠናቀቁን ይቆጣጠራል፣ የተፈቀደውን የትርፍ ሰዓት ክፍያ አፈፃፀም ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

3/ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ከፍተኛ ወጪ ሊያስከትል ስለሚችል በትርፍ ሰዓት አፈቃቀድ ላይ ኃላፊነት የተሞላበት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

4/ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሊሠራ የሚችል ሥራ በትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲሠራ ማድረግ ተገቢነት የለውም፡፡

5/ አንድን ሠራተኛ በአንድ ወር ውስጥ ከ120 ሠዓት በላይ ማሠራት አይቻልም፡፡

6/ ሥልጣን ያለው መሥሪያ ቤት መመሪያው በሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለትርፍ ሰዓት ክፍያ የወጣውን ሂሣብ ለመመርመር ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ለምርመራው የሚያግዙ ሰነዶችን የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

7/ የትርፍ ሠዓት ሥራ አፈፃፀም በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መስሪያ ቤት የትርፍ ሠዓት ሥራ የሠሩ ሠራተኞችና ክፍያ የተከፈላቸውን ሠራተኞች ብዛትና የተከፈለ የብር መጠን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሚቀጥለው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት መጨረሻ ቀን ድረስ የመንግሥት መ/ቤቱ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የመላክ ግዴታ አለበት፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

## 9. የትርፍ ሰዓት ሥራ የክፍያ ሂሣብ ስሌት እና አከፋፈል፡-

1/ አንድ ሠራተኛ በወር የሚያገኘው ደመወዝ ለ30 ቀናት ሲካፈል በአንድ ቀን የሚያገኘውን ደመወዝ፣ በቀን የሚገኘው ደመወዝ ደግሞ ለ8 ሰዓት ሲካፈል በአንድ ሰዓት የሚከፈለውን ደመወዝ ይሰጣል፡፡ በዚህም መሠረት አንድ የትርፍ ሰዓት ሥራ የሚሠራ ሠራተኛ ቢያንስ ከመደበኛ ደመወዙ በተጨማሪ፣

ሀ/ ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት የሚሠራ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለመደበኛ ሥራ በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.25 ተባዝቶ፣

ለ/ በሥራ ቀኖች ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰዓት የሚሠራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለው ደመወዝ በ1.5 ተባዝቶ፣

ሐ/ በሳምንቱ የእረፍት ቀናት የሚሠራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈለውደመወዝ በ2.00 ተባዝቶ፣

መ/ በህዝብ በዓላት ቀናት የሚሠራ የትርፍ ሰዓት ሥራ በሰዓት የሚከፈል ደመወዝ በ2.50 ተባዝቶ አበሉ ይከፈለዋል፡፡

## 10. የሾፌሮች ትርፍ ሰዓት ሥራ አበል ክፍያ፡-

1/ ሾፌሮች ከሥራቸው ልዩ ባህርይ በመነሳት ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ.30/ጠ13/46/1010 በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት የበላይ አመራር ሾፌር ትርፍ ሰዓት ሥራ አበል ክፍያ ብር 800 (ስምንት መቶ ብር) የነበረው ብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር)፣ የሌሎች ሾፌሮች ትርፍ ሰዓት ሥራ አበል ክፍያ ብር 600 (ስድስት መቶ ብር) የነበረው ብር 1300 ( አንድ ሺ ሦስት መቶ ብር) መከፈል አለበት፡፡

2/ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ፕሬዚዳንቶች እና ምክትል ፕሬዜዳንቶች ሾፌሮች ትርፍ ሰዓት ሥራ አበል ክፍያ ይከፈላቸው የነበረው ብር 900 (ዘጠኝ መቶ ብር) ብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) የሌሎች

...ቶሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ሾፌሮች ትርፍ ሰዓት ሥራ አበል ክፍያ ብር 800 (ስምንት መቶ ብር) የነበረው ብር 1300 መከፈል አለበት፡፡

3/ ለሾፌር ረዳቶች ተፈቅዶ የነበረው ትርፍ ሰዓት ሥራ አበል ክፍያ ብር 400 (አራት መቶ ብር) ብር 800 (ስምንት መቶ ብር) መከፈል አለበት፡፡

11. የጥበቃ ስራ በትርፍ ሰዓት ሥራ የማይከናወን ስለመሆኑ፡-

1/ በአዋጅ ቁጥር 1064/2010 የመንግሥት ሠራተኞች መደበኛ የሥራ ሰዓት እንደሥራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በሣምንት ከ39 ሰዓት መብለጥ የለበትም ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት የጥበቃ ሠራተኞች በሳምንት ከ39 ሰዓት የበለጠና የተራራቀ ሰዓት መሥራት ስለማይኖርባቸው ቢያንስ 24 ሰዓት ሰርተው 48 ሰዓት ማረፍ ይጠበቅባቸዋል፣

2/ የጥበቃ ሥራ በትርፍ ሰዓት ክፍያ አይስተናገድም፣

3/ ለጥበቃ ሥራ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል መጠን ተቋሙ የሚሟላት ግዴታ አለበት፡፡

12. **የትርፍ ሰዓት ክፍያ የማይከፈልባቸው ሁኔታዎች ፡-**

1/ በማንኛውም ቀን እስከ 1:00 ሰዓት የተከናወነ የትርፍ ሰዓት ሥራ እንደትርፍ ሰዓት ስራ ተቆጥሮ ክፍያ መፈጸም አይቻልም፣

2/ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሥራ በተሰራ በ3 ወር ውስጥ መከፈል አለበት፣

3/ በ3 ወር ውስጥ ያልተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ አይፈፀምበትም፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

# ክፍል 3

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**13. የተሻሩ መመሪያዎች**

1/ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ20/ጠ13/36/8/3 የትርፍ ሰዓት ስለሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች የወጣው መመሪያ፣

2/ ጥር 19 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ30/ጠ13/46/1010 የሹፌሮችን ቁርጥ አበል በተመለከተ የተላለፈው ሰርኩላር እና

3/ ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/814 የጥበቃ ሠራተኞች የሥራ ሰዓት ማሻሻያን በተመለከተ የተላለፈው ሰርኩላር በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡

**14.ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**15. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ኮሚሽኑ መመሪያውንም ሆነ በመመሪያው ውስጥ የተሸፈኑ አንቀፆችን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሻል ይችላል፡፡

**16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

መመሪያው በኮሚሽኑ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መኩሪያ ኃይሌ (ፒ ኤች ዲ)**

**የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር**